የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 43
ADDIS ABABA-11th May, 2004

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፬፻፪/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ..........
ገጽ ፪ሺ፮፻፳፱

**CONTENTS**

**Proclamation No. 402/2004**

**Cooperative Societies (Amendment) Proclamation ..**
**.............. Page 2629**

### አዋጅ ቁጥር ፬፻፪/፲፱፻፺፮

### የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ ማሻሻያ አዋጅ

የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ማሻ ሻያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፪/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ማሻሻያ**

የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል:

፩/ ከአንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ ፭ ቀጥሎ የሚከ ተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች /፮/፣ /፯/፣ /፰/፣ /፱/ ተጨምረዋል፤

### PROCLAMATION NO. 402 /2004.

### COPPERATIVE SOCIETIES (AMENDMENT) PROCLAMATION

**WHEREAS,** it is necessary to amend cooperative societies proclamation No. 147/1998;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Cooperative Societies (Amendment) Proclamation No. 402/2004."

**2. Amendments**

Cooperative Societies Proclamation No.147/1998 shall be amended as follows.

1. The following new Sub Articles (6), (7), (8) and (9) are added after Sub Articles 5 of Articles 9:

“፮/ ቢዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበ ማንኛውም ሕብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ተጨማሪ ንግድ ፈቃድ ሳያስፈልገው በማንኛውም የንግድ ሥራ ላይ መሰማራት ይችላል::

፯/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፪ /ሀ/ እስከ /ሰ/ የተዘረዘሩት መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥ ከአንድ አመት ሳልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት ሰጥቶ የተቀሩት መስፈርቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲሟሉ ማስደረግ ይችላል::

፰/ ማንኛውም ማህበር ከተቋቋመበት አላማና መርህ ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በዚህ ሕግ የተፈቀደለትን ሥራ እንዳይሠራ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ሊታገድ ይችላል::

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ መሠረት የታገደ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ዕግዱ እንዲነሳለት አገግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል:: ጥያቄውን የተቀበለው አግባብ ያለው ባለሥልጣን የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ዕግዱ እንዲነሳለት ያቀረበው ምክንያት በቂና አግባብ ሆኖ ሲገኝ እግዱን ሊያነሳ ይችላል:: አግባብ ያለው ባለሥልጣን እግዱን ያላነሳ እንደሆነ ያላነሳበትን ምክንያት ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በጽሑፍ ያሳውቃል:: አግባብ ያለው ባለሥልጣን ባቀረበው ምክንያት ያልተስማማ ጠቅላላ ጉባኤ የዳኝነት ሥልጣን ላለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል:: ”

፪/ አንቀጽ ፲፮/፩ – ፫/ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፮ ተተክቷል፤

“አንቀጽ ፲፮ ስለዕጣ ክፍያ

፩/ ማንኛውም ማህበር ሥራውን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን ካፒታል ማግኘት እንዲችል እኩል ዋጋ እና ብዛት ያላቸውን ዕጣዎች በጠቅላላ ጉባኤ አስወስኖ እንዲሸጡ ያደርጋል::

“ 6. Any cooperative society which has been legally registered pursuant to Sub Articles 3 of this Article shall engage in any business as of the date of registration without the necessity of securing additional trade license.

7. Where the appropriate authority ensures that requirements indicated under Sub Article 2(a)-(g) are met, it shall grant temporary certificate which may serve not more than a year and shall cause the rest requirements to be observed within a specified period of time.”

8. Where any society is found operating out of the objectives for which it is established, it may be suspended by the appropriate authority from carrying out activities permitted by this law.

9. Where the general assembly of a society suspended pursuant to Sub Articles 8 of this Article submits its request to reverse the decision for suspension and where the appropriate authority found the request appropriate, it may reverse the decision for suspension. Where the appropriate authority did not reverse the suspension it shall give a written explanation to the General Assembly of the society. The General Assembly may appeal to the higher court which has jurisdiction on the decision made by the appropriate Authority.”

**2. Articles 16(1)-(3) is hereby deleted and replaced by the following new**

**“Article 16: Payment of shares**

1/ Any cooperative society shall, after securing the decision of the general assembly, sell shares that shall have equal number and parvalue with the view to enable the society to obtain capital necessary to start its function.

፪/ ማንኛውም ማህበር ሲመሠረት በጠቅላላ ጉባኤ እንዲሸጥ ከተወሰነው የዕጣ መጠን ውስጥ ቢያንስ ፩/፭ኛው ከአባላት ይሰበሰባል፡፡ እንደዚሁም ቀሪውን ዕጣ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አራት ዓመታት ውስጥ መሸጥ ይኖርበታል፡፡

፫/ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት እንዲሸጥ የተወሰነ የዕጣ መጠን ሲጠናቀቅ ተጨማሪ ካፒታል ካስፈለገ ተጨማሪ ዕጣዎች እንዲሸጡ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት እንደገና ሊወስን ይችላል፡፡

፬/ ማህበሩ የሚሸጠው ዕጣ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚከፈል ሊሆን ይችላል፡፡ በዓይነት የሚከፈል ዕጣ መጠን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

፭/ አንድ አባል በጠቅላላ ጉባኤ እንዲሸጥ ከተወሰነው የዕጣ መጠን ውስጥ ከ፲ ከመቶ በላይ ድርሻ ሊኖረው አይችልም፡፡

፮/ የካፒታል እጥረት ያጋጠመው ማህበር የማህበሩን መርህ በማይቃረን ሁኔታ የተወሰነ ዕጣ የማህበሩ አባል ላልሆነ ሰው መሸጥ ይችላል፡፡

፯/ ከአባላት ውጭ ላለ ሰው የሚደረገው የዕጣ ሽያጭ ዝርዝር ሁኔታ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

፫/ ከአንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፫/፣ /፬/ ተጨምረዋል፡፡

"፫/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማንኛውም ማህበር ከንብረቱ ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት ላለበት ክርክር ከሚከፈል የዳኝነት ክፍያ ነፃ ሊያደርገው ይችላል፡፡

፬/ አንድ ማህበር ከንብረት ጋር በተያያዘ በሚፈጽመው ውል የሚመነጭ መብት ከ፳ ዓመት በኋላ ቀሪ ይሆናል፡፡

2/ Any cooperative society shall collect, upon its formation from the members at least 1/5 of the amount of the share that the general assembly has decided to be sold. And it shall sell the rest of the shares within four years as of the time of its establishment.

3/ Where the need for additional capital is arose, upon completion of the sell of shares in accordance with the decision of the general assembly, the general assembly may decide once again for the sell of additional shares in accordance with Sub article 1 of this Article.

4/ The share that the society sells may be sold either in cash or in kind. Shares paid in kind shall be determined by the by-law of the society.

5/ Any member may not hold more than 10% of shares out of those that the general assembly decide to be sold.

6/ A society which faces shortage of capital may sell certain shares to a person who is not a member of the society without contradicting the principle of the society.

7/ Particulars as regards to manner of sale of shares to a person who is not member to the society shall be determined by the by-laws of the society."

3. The following new Sub Articles (3) (4) are added after Sub Articles (2) of Article 31.

"3) he Council of Ministers may make any society free from any court fees that is payable in connection with dispute entertained by courts.

4) Any right emanated from a contract concluded by the society involving its properties shall be barred by statute of limitation after 20 years.

**፬/ አንቀጽ ፴፫/፩ – ፪/ ተሽሮ በዚህ አዲስ አንቀጽ ፴፫ ተተክቷል።**

"፩/ አንድ ማህበር ከተጣራ ትርፍ ላይ ፴ በመቶ እየቀነሰ በመጠባበቂያ ሂሳብ ያስቀምጣል። በመጠባበቂያው ሂሳቡ የሚቀመጠው ከማህበር ካፒታል ፴ በመቶ እስኪሞላ ድረስ ነው።

፪/ ከመጠባበቂያ የሚቀረው የተጣራ ትርፍ አደላደል በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል።

፫/ አባላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ከሚያገኙት የተጣራ ትርፍ ውስጥ ተጨማሪ ዕጣ ሊገዙበት ይችላሉ።"

**፭/ የአንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ ፪ ተሽሯል።**

**፮/ ከአንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ ፪ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች /፫/፣ /፬/ ተጨምረዋል።**

፫/ ፍርድ ቤት እንዲፈርስ ሲወስን።

፬/ በማህበሩ የሂሳብ ምርመራ ውጤት መሠረት የከሰረና የኪሳራውም መጠን ማህበሩን ህልውና የሚያሳጣ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥና በጠቅላላ ጉባኤ ሲወስን።

**፯/ የአንቀጽ ፵ /፫/ ፵ /፭/ ሆኗል።**

**፰/ አንቀጽ ፵፮ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል።**

**"አንቀጽ ፵፮ ጉዳዮችን በዕርቅ ስለመጨረስ**

፩/ በአንቀጽ ፵፱ የተመለከቱት ክርክሮች ለሽምግልና ዳኝነት ከመቅረባቸው በፊት ተከራካሪ ወገኖች በሚመርጡት ሦስተኛ ወገን በእርቅ መታየት ይችላል።

**4. Articles 33(1) and (2) are deleted and replaced by the following new Article 33**

"1) any cooperative society shall deduct 30% of the net profit and allocate for the reserve fund. The amount allocated for the reserve fund shall nor exceed 30% of the capital of the society and it shall be deposited in the saving account of the society

2) The distribution of the remaining net profit shall be determined by the general assembly.

3) Any member who has received net profit as per Sub Article 2 this Article can buy an additional share."

**5. Sub 2 of Article 34 is deleted.**

**6. The following new Sub-Articles (3) and (4) are added after Sub Articles (2) of Article 40.**

"(3) Where the court decides for its dissolution.

(4) Where the auditing reveals that it is bankrupt and when the appropriate authority ensures that causes the dissolution and the general assembly decides."

**7. Article 40(3) shall become Article 40(5).**

**8. Article 46 is deleted and replaced by the following new Article.**

**"46. Settling disputes through conciliation**

1/ Disputes indicated under Article 49 may be settled through reconciliation of parties elected by disputants before they are submitted to arbitration.

፪/ እያንዳንዱ ወገን አንድ አስታራቂ ይመርጣል፣ የአስታራቂዎች ሰብሳቢ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ይመረጣል::

፫/ የአስታራቂዎችን ሰብሳቢ ለመምረጥ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ያልደረሱ እንደሆነ ሰብሳቢው አግባብ ባለው ባለሥልጣን ይመረጣል::

፱/ አንቀጽ ፶፰/፪/ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፶፰/፪/ ተተክቷል::

"፪/ በገበሬዎች የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፹፯ መሠረት ተቋቁመው በመሥራት ላይ ያሉ ማህበራት በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ተመዝግበው ሥራቸውን ያከናውናሉ::"

፲/ ይህ አዲስ አንቀጽ ፶፱/ ተብሎ ተጨምሯል

አንቀጽ ፶፱ የመተባበር ግዴታ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በተደነገጉት ጉዳዮች ላይ የሚመለከተው አካል የመተባበር ግዴታ አለበት::

፲፩/ አንቀጽ ፶፱/ አንቀጽ ፷/ ሆኗል::

፲፪/ "አንቀጽ ፷፩ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::"

አዲስ አበባ ግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



2/ Each party shall elect a reconciliation; the chairperson of the reconciliation shall be elected in accordance with the agreement of the two parties.

3/ Where the two parties failed to reach agreement to elect the chairperson of the reconcili- ation, the chairperson shall be elected by the appropriate authority."

**9. Articles 58(2) is deleted and replaced by the following new Article 58(2)**

"(2) Agricultural cooperative societies, which were established pursuant to Proclamation No.85/1995 and which are still operating shall be registered once again in accordance with this Proclamation."

**10. The following new Articles added as Articles 59**

"59. Obligation to cooperate
Any concerned organ shall have the obligation to cooperate on matters provided in this Proclamation."

**11. Article 59 shall become Article 60**

**12. "61 Effective Date**

The Proclamation shall come into force on 11th date of May., 2004."

**Done at Addis Ababa, 11th day of May, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**